# [በኤሊባቡር ከ20 በላይ ዐማሮች በአንድ ቀን ብቻ በገጀራ ተጨፍጭፈው ተገድለዋል]

October 21, 2017

**ከሙሉቀን ተስፋው**

በኤሉ አባ ቦራ (ኤሊባቡር) ዞን ደጋና ጮራ ወረዳዎች የዐማራ ተወላጆች ተለይተው እየተጠቁ እንደሆኑ የተጎጅ ቤተሰቦች ትናንት ጥቅምት 11 ቀን 2010 ዓ.ም. በስልክ አረጋግጠዋል፡፡ መንግሥትን በመቃወም የተጀመረው የተቃውሞ ሰልፍ ዐማሮችን በጅምላ መግደልና ቤትና ንብረታቸውን ወደ ማውደም መዞሩን የሚግልጹት ተጎጂዎች ትናንት ብቻ በአንድ ቀን ከ10 በላይ ሰዎች በገጀራ ተጨፍጭፈው ተገድለዋል፡፡

የዐማራ ተወላጆች ቤትና ንብረት እየወደመ እንደሆነ የሚናገሩት በተለይ በደጋ ወረዳ ጎሮ፣ ሰፌና ደፎ ቀበሌዎች የዐማራ ቤትና ንብረት ሙሉ በሙሉ ወድሟል፤ በዐሥር ሺህዎች የሚቆጠሩ ዐማሮችም በጫካ ተዘርተው እንደሚገኙ ገልጸውልናል፡፡ የኦሮሚያ ፖሊስ ዩኒፎ




ርም የለበሱ ሰዎች የግድያው ዋና ተሰላፊ እንደነበሩም አክለው ገልጸዋል፡፡

ለጊዜው በጎሮ ቀበሌ የተገደሉ 6 ያክል ሰዎች ስም ዝርዝር የደረሰን ሲሆን የተቆራረጡ የዐማራ አስከሬኖች ሁሉ በጮራ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ ተከማችቶ እንደሚገኝም ተገልጧል፡፡ ትናንት ከተገደሉ ሰዎች መካከል

1. አቶ ክንዱ
2. አቶ ምስጋናው የዚህ ግለሰብ ገዳይ የክልሉ ልዩ ኃይል ፖሊስ አባል ነው፤
3. አቶ ሙላት
4. አቶ ባቡ
5. አቶ ይማም
6. ሼህ ሁሴን ናቸው፡፡

በኤሌባቡር ጫካዎች ተዝርተው የሚገኙ ዐማሮች የድረሱልን ጥሪም አስተላልፈዋል፡፡



Veronica Melaku is with Suleiman Dedefo and Addisu Arega Kitessa. •••

Just now ·

በኢሊባቦር የምንሰማው የአማራ ግድያ ምንም ልንታገሰው የማንችል መሆኑን ማሳወቅ እፈልጋለሁኝ። የዚህ ግድያ መሀንድሱ እና አርክቴክቱ ህውሃት ይሁን እንጂ ኦህዴድም "ከደሙ ንፁህ ነኝ " ብሎ እጁን ሊታጠብ ፈፅሞ አይችልም ።
የአሁኑ አዲሱ የኦሮሚያው ተቃውሞ በአምቦ ፣ በሻሸመኔ እና በተለያዩ ከተሞች በሰላም ተጀምሮ በሰላም እስኪጠናቀቅ ሲያጅብ የነበረው የኦሮሚያ ልዩ ሀይል እንደት የኢሊባቦርን ጭፍጨፋ ማስቆም አልቻለም ? ኦፒድኦ ለዚህ መልስ አለው ወይ ?

ይሄ ሰልፍ ገና ሲጀመር ከሁለት ሳምንት በፊት ጀምሮ ጃዋር መሀመድና የኦሮሞ ዋና አክቲቪስቶች "ወያኔ የሚዘውረው ሰልፍ ነው " ብለው ስላስጠነቀቁ እነሱን ተጠያቂ ማድረግ አይቻልም ነገር ግን የኦሮሞ ብሄርተኞች ባላቸው መዋቅር በአስቸኳይ ይሄን ጉዳይ አጣርተው ግልፅ ሊያደርጉ ይገባል።
ራሳቸውን መከላከል የማይችሉ ፣ ያልታጠቁና ያልተደራጁ ንፁሃን አማሮችን መግደል ሳይውል ሳያድር ከፍተኛ ዋጋ እንደሚያስከፍላችሁ በእርግጠኝነት ማስጠንቀቅ እፈልጋለሁኝ።